# ዲጂታል ወደ አናሎግ ቀያሪ ሣጥንዎን ከቪሲአር ጋር ማገናኘት

# FCC የተጠቃሚዎች መረጃ

አናሎግ ቴሌቪዥኖችና የቪዲዮ መቅረጫዎች (ቪሲአሮች) ከችርቻሮ መደብሮች ሊገዛ በሚችል "ከዲጂታል ወደ አናሎግ ቀያሪ ሣጥን" አማካኝነት የዲጂታል ቴሌቪዥን (ዲቲቪ) የሥርጭት ሞገዶችን መቀበል ይችላሉ። አንድ ቀያሪ ሣጥን ተጠቅመው ቁ.1 ላይ በተመለከተው መሠረት ገጠማዎችን ካደረጉ፤ በአንድ ጊዜ አንድ ቻነል መመልከትና መቅረጽ ይችላሉ። ሁለት ቀያሪ ሣጥኖችን በመጠቀም በቁ.2 ላይ የተመለከተውን አገጣጠም ከተገበሩ፤ አንድን ቻነል እየተመለከቱ ሌላ አንድ ቻነል መቅረጽ ይችላሉ።


## ገጠማ ቁ.1፡- አንድን ቻነል እየተመለከቱ መቅረጽ

**ዕቃዎች፡-** አናሎግ ቴሌቪዥንዎ፣ አናሎግ ቪሲአርዎ፣ አሁን እየተጠቀሙበት ያለው አንቴና (የውስጥም ሆነ የውጭ) እንዲሁም አንቴናዎን ከቪሲአርዎ ጋር የሚያገናኙበት ኮአግዚያል ሽቦ (በቀኝ በኩል ምስሉ የተመለከተው) አስፈላጊ ናቸው። አዲሱ ቀያሪ ሣጥንዎ ሁለተኛ ኮአግዚያል ሽቦና የርቀት መቆጣጠሪያ ይኖረዋል። ገጠማውን ከመጀመርዎ አስቀድመው የቲቪዎንና የቪሲአርዎን ዋና የኃይል መቀበያ ሶኬቶች መንቀል ይኖርብዎታል።



Coaxial Wire

ደረጃ ❶ ያለዎትን ኮአግዚያል የአንቴና ሽቦ "Antenna In (RF)" ከሚለው የቪሲአርዎ መሰኪያ ክፍል ላይ ይንቀሉ።


ቪሲአርዎን እና ቲቪዎን የሚያገናኘውን ሽቦ እንዳለ ይተዉት (የድምጽ/የምስል ኬብልም ሆነ ኮአግዚያል ሽቦ)።




ደረጃ ❷ ኮአግዚያል ሽቦውን “Antenna In (RF)” በሚለው በመቀየሪያ ሣጥንዎ ላይ የሚገኝ መሰኪያ ላይ ይሰኩት።




ደረጃ ❸ ከመቀየሪያ ሣጥኑ ጋር አብሮ የመጣውን ኮአግዚያል ሽቦ በመጠቀም አንደኛውን ጫፍ “Out To TV (RF)” በሚለው በመቀየሪያ ሣጥንዎ ላይ የሚገኝ መሰኪያ ላይ ይሰኩት። ሌላኛውን ጫፍ ደግሞ “Antenna In (RF)” በሚለው የቪሲአርዎ መሰኪያ ላይ ይሰኩት።





ደረጃ ❹ የመቀየሪያ ሣጥንዎን፣ የቪሲአርዎንና የቲቪዎን የኃይል መቀበያ ሶኬት ይሰኩና መሣሪያዎቹን ያብሩ። ቪሲአርዎን በቻነል 3 ወይም 4 ላይ ካደረጉ በኋላ (በመቀየሪያ ሣጥኑ የአጠቃቀም መመሪያ ላይ

FCC
Federal Communications Commission ▪ Consumer & Governmental Affairs Bureau ▪ 445 12th St., SW ▪ Washington, DC 20554
1-888-CALL-FCC (1-888-225-5322) ▪ TTY: 1-888-TELL-FCC (1-888-835-5322) ▪ Fax: 1-866-418-0232 ▪ www.fcc.gov/cgb




የተመለከቱትን የአጠቃቀም መመሪያዎች ይከተሉ) ቲቪዎ ከቪሲአሩ የሚላውን ምስል እንዲቀበል ያድርጉት፡፡ ከቀያሪ ሣጥኑ ጋር አብሮ የቀረበልዎትን የርቀት መቆጣጠሪያ ተጠቅመው በስክሪኑ ላይ የተመለከቱትን የማስተካከያ መመሪያዎች በመተግበር በመሠራጨት ላይ ያሉ የዲቲቪ ጣቢያዎችን ፈልገው ካገኙ በኋላ የዲጂታል ቴሌቪዥን ጠቃሚ ገጽታዎችን መከታተል ይችላሉ! በቀያሪ ሣጥንዎ አማካኝነት እየተመለከቱ ያሉትን ፕሮግራም መቅረጽ ይችላሉ፡፡



## ገጠማ ቁ.2፡- አንድን ቻነል እየተመለከቱ ሌላ ቻነል መቅረጽ



ድ/ም ኬብሎች ኮአግዚ. ሽቦ

**ዕቃዎች፡-** አናሎግ ቲቪዎ፣ እየተጠቀሙበት ያሉት አንቴና (የውስጥም ሆነ የውጭ)፣ አንቴናዎን ከቴሌቪዥንዎ ጋር ያገናኙበት ኮአግዚያል ሽቦ (በቀኝ ጥግ በኩል ምስሉ የተመለከተው)፣ ተጨማሪ አራት ኮአግዚያል ሽቦዎች፣ የድምጽ/ምስል ኬብሎች (ምስላቸው በቀኝ በኩል የተመለከተው)፣ ባለ 2-መስመር ስፐሊተር እና ሁለት ቀያሪ ሣጥኖች አስፈላጊ ናቸው፡፡ አዲሶቹ ቀያሪ ሣጥኖችዎ እያንዳንዳቸው አንድ ኮአግዚያል ሽቦ፣ የድምጽ/ምስል ኬብሎች ስብስብ (ቀይ፣ ነጭ ቢጫ ተሰኪ ያላቸው ሦስት ሽቦዎች) እንዲሁም አንድ የርቀት መቆጣጠሪያ ይኖራቸዋል፡፡ ገጠማውን ከመጀመርዎ አስቀድመው የቲቪዎንና የቪሲአርዎን ዋና የኃይል መቀበያ ሶኬቶች መንቀል ይኖርብዎታል.

<table>
<tr><td>ደረጃ ❶ ያለዎትን ኮአግዚያል የአንቴና ሽቦ "Antenna In (RF)" ከሚለው የቪሲአርዎ መሰኪያ ክፍል ላይ ይንቀሉ፡፡<br><br>ደረጃ ❷ ቁ.2 ኮአግዚያል ሽቦውን "To TV (RF)" ከሚለው የቪሲአርዎ መሰኪያ ክፍል ላይ ይንቀሉ፡፡ ሌላኛውን የሽቦ ቁ.2 ጫፍ በቲቪው ላይ እንደተሰካ ይተዉት፡፡</td><td></td></tr>
<tr><td>ደረጃ ❸ ኮአግዚያል የአንቴና ሽቦውን በባለ 2-መስመር ስፐሊተሩ ላይ በሚገኘው "In" የሚል መሰኪያ ላይ ይሰኩት፡፡</td><td></td></tr>
<tr><td>ደረጃ ❹ የተላቀቀውን የሽቦ ቁ.2 ጫፍ "Out to TV (RF)" በሚለው የመቀየሪያ ሣጥን "ሀ" መሰኪያ ላይ ይሰኩ፡፡<br><br>ደረጃ ❺ የኮአግዚያል ሽቦ ቁ.3ን አንደኛ ጫፍ በባለ 2-መስመር ስፐሊተሩ ላይ ከሚገኙት "Out" የሚሉ መሰኪያዎች በአንዱ ላይ ይሰኩት፡፡ ሌላኛውን ጫፍ</td><td></td></tr>
</table>

<table>
<tr><td>"Antenna In (RF)" በሚለው የመቀየሪያ ሣጥን "ሀ" መሰኪያ ላይ ይሰኩት።</td><td></td></tr>
<tr><td>ደረጃ ❻ የኮአግዚያል ሽቦ ቁ.4ን አንደኛ ጫፍ በሌላኛው "Out" የሚል በባለ 2-መስመሪ ስፕሊተሩ ላይ የሚገኝ መሰኪያ ላይ ይሰኩት። ሌላኛውን ጫፍ "Antenna In (RF)" በሚለው የቀያሪ ሣጥን "ለ" መሰኪያ ላይ ይሰኩት።<br><br>ደረጃ ❼ የኮአግዚያል ሽቦ ቁ.5ን አንደኛ ጫፍ በመቀየሪያ ሣጥን "ለ" ላይ በሚገኘው "Out to TV (RF)" የሚል መሰኪያ ላይ ይሰኩት። ሌላኛውን ጫፍ "Antenna In (RF)" በሚለው የቪሲአርዎ መሰኪያ ላይ ይሰኩት።</td><td>
</td></tr>
<tr><td>ደረጃ ❽ የድምጽ/ምስል ኬብሎችዎን በመጠቀም የኬብሎቹን አንደኛ ጫፍ በቪሲአርዎ ላይ በሚገኙት "A/V Out" የሚሉ መሰኪያዎች ላይ ይሰኩት። የተሰኪዎቹን ቀለማት ከመሰኪያዎቹ ቀለማት ጋር አንድ ዓይነት በማድረግ ቀዩን በቀዩ ላይ፣ ነጩን በነጩ ላይ፣ ቢጫውንም በቢጫው ላይ ይሰኩ። ሌላኛውን የኬብሎቹን ጫፍም በተመሣሣይ አኳኋን በቲቪዎ ላይ በሚገኘው "A/V In" የሚል መሰኪያ ላይ ይሰኩት። ቲቪዎ ቀይ (Audio R) የሚል መሰኪያ ከሌለው፤ የቀዩን ኬብል ሁለቱንም ጫፎች አይሰኳቸው።</td><td>
</td></tr>
<tr><td colspan="2">ደረጃ ❾ የቀያሪ ሣጥኖችዎን፣ የቪሲአርዎንና የቲቪዎን ዋና የኃይል መቀበያ ሽቦዎች በመሰካት ሁሉንም ያብሯቸው። የቲቪዎን ቻነል በቻነል 3 ወይም 4 ላይ በማድረግ (የቀያሪ ሣጥኑን የአጠቃቀም መመሪያዎች ይከተሉ) ቀያሪ ሣጥን "ሀ"ን ለማስተካከል ይዘጋጁ። ከቀያሪ ሣጥን "ሀ" ጋር አብሮ የቀረበልዎትን የርቀት መቆጣጠሪያ ተጠቅመው በስክሪን ላይ የሚሰጥዎትን የማስተካከያ መመሪያ በመከተል በሥርጭት ላይ የሚገኙ የዲቲቪ ቻነሎችን ይፈልጉ።<br><br>ደረጃ ❿ ቲቪዎን "Audio/Video In" ላይ በማድረግና ቪሲአርዎን በቻነል 3 ወይም 4 ላይ በማስተካከል (የቀያሪ ሣጥኑን የአጠቃቀም መመሪያዎች ይከተሉ) ቀያሪ ሣጥን "ለ"ን ለማስተካከል ይዘጋጁ። ከቀያሪ ሣጥን "ለ" ጋር አብሮ የቀረበልዎትን የርቀት መቆጣጠሪያ ተጠቅመው በስክሪን ላይ የሚሰጥዎትን የማስተካከያ መመሪያ በመከተል በሥርጭት ላይ የሚገኙ የዲቲቪ ቻነሎችን ይፈልጉ።</td></tr>
</table>

- **አንድን ፕሮግራም በቪሲአርዎ ለመቅረጽ ከፈለጉ፤ የቪሲአርዎን ቻነል በቻነል 3 ወይም 4 ላይ በማድረግ የቀያሪ ሣጥኑን ጣቢያ መፈለጊያ በሚፈልጉት ቻነል ላይ ያድርጉት።**
- **ቀያሪ ሣጥንዎ "ዩኒቨርሳል የርቀት መቆጣጠሪያ" ካለው አልያም ዩኒቨርሳል የርቀት መቆጣጠያ ያለዎት ከሆነ፤ ከቀያሪ ሣጥንዎ ጋር የተሰጠዎትን መመሪያ ተከትለው የርቀት መቆጣጠሪያዎ ለቲቪው፣ ለቪሲአሩና ለቀያሪ ሣጥኑ ማገልገል እንዲችል ፕሮግራም ያድርጉት።**
- **የዲቪዲ መቅረጫ ወይም ዲቪአር ካለዎትም ከላይ የተመለከቱትን የተግባር ደረጃዎች በመጠቀም ማገናኘት ይችላሉ።**

ስለ ዲቲቪ ሽግግር ተጨማሪ መረጃዎችን ለማግኘት www.dtv.gov ድረ ገጽን መጎብኘት ወይም በኢሜይል አድራሻ dtvinfo@fcc.gov ፤ በስ.ቁ. 1-888-CALL-FCC (1-888-225-5322) ለድምጽ ጥሪ ወይም በ1-888-TELL-FCC (1-888-835-5322) ቲቲዋይ፤ በፋክስ ቁ. 1-866-418-0232 ወይም በሚከተለው አድራሻ በመጻፍ FCCን ማግኘት ይችላሉ።

Federal Communications Commission
Consumer & Governmental Affairs Bureau
Consumer Inquiries and Complaints Division
445 12th Street, SW
Washington, DC 20554

*ይህንን ወይም ሌሎች በተለያ መንገድ ለተጠቃሚዎች የተዘጋጁ መረጃዎችን (በኤሌክትሮኒክ ኤኤስሲአይአይ ጽሑፍ፣ በብሬይል፣ በትልልቅ ሕትመቶች፣ ወይም በድምጽ የተዘጋጁ መረጃዎችን) ለማግኘት ቀጥሎ የተመለከተውን አድራሻ ወይም የስልክ ቁጥር መጠቀም ወይም በFCC504@fcc.gov የኢሜይል መልዕክትዎን መላክ ይችላሉ።*

*በዚህና በሌሎችም የኤፍሲሲ የተጠቃሚዎች ርዕሰ ጉዳይ ዙሪያ መረጃዎችን በኮሚሽኑ ኤሌክትሮኒካዊ የደንበኛ አገልግሎት አማካኝነት ለማግኘት ይህን ይጫኑ*
*http://www.fcc.gov/cgb/contacts/*

*ይህ ሰነድ ተጠቃሚዎችን ለማስተማር ዓላማ ብቻ የተዘጋጀና በውስጡ በተመለከተው ርዕሰ ጉዳይ ወይም ተዛማጅ ጉዳዮች ላይ ተጽዕኖ የማሳደር ዓላማ የሌለው ነው።*